## *በ2018 ዓ.ም በኢትዮጵያ ፐብሊክ ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በቅድመ ምረቃ መርሀ-ግብር በትምህርት ሚኒስቴር ለተመደባችሁ ተማሪዎች በሙሉ*

በ2017 ዓ.ም የአስራ ሁለተኛ ክፍል ሀገራዊ የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና ወስዳችሁ የማለፊያ ውጤት ያስመዘገባችሁ እና በ2018 ዓ.ም በኢትዮጵያ ፐብሊክ ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በትምህርት ሚኒስቴር የተመደባችሁ አዲስ የቅድመ ምረቃ መደበኛ መርሀ-ግብር ተማሪዎች በሙሉ ዩኒቨርሲቲያችን እንኳን ደስ አላችሁ እያለ የመመዝገቢያ ቀን ጥቅምት 6 እና 7 2018 ዓ.ም መሆኑን አውቃችሁ በዕለቱ በአካል በመቅረብ ሪፖርት እንድታደርጉ እናሳስባለን፡፡

ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲው ስትመጡ፡-

1. ሀገራዊ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ሰርትፊኬት ዋናውና ኮፒ፣
2. ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ትራንስክሪፕት ዋናውና ኮፒ፣
3. የ8ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ሰርትፊኬት፣
4. ፓስፖርት ሳይዝ (3 በ4) ፎቶግራፍ፣
5. የፋይዳ መታወቂያ ዋናውና ኮፒ፣
6. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር/TIN Number/፣
7. የግል መገልገያ የሆኑትን ማለትም ብርድ ልብስ፣ አንሶላ፣ትራስ ልብስ እና የስፖርት ትጥቅ፣

ይዛችሁ መምጥጣት ይጠበቅባችኋል፡፡

**ማሳሰቢያ ፡-**

- ከተጠቀሰው ዕለት ቀድሞም ሆነ ዘግይቶ የሚመጣን ተማሪ የማናስተናግድ መሆኑን እንገልጻለን፡፡
- ጥቅምት 6 እና 7፣ 2018 ዓ.ም ከማለዳ ሁለት ሰዓት እስከ ቀትር 10 (አስር) ሰዓት በ4 መዉጫ በሮች ባሉ መናኸሪያዎች ማለትም ከአውቶብስ ተራ (መርካቶ) ፣ ከቃሊቲ መናኻሪያ፣ ከአየር ጤና መናኸሪያ እና ከላምበረት መናኻሪያ ባሉ ቦታዎች እናንተን ለመቀበል አውቶብሶችን አዘጋጅተን የምንጠብቃችሁ መሆኑን ከወዲሁ እናሳስባለን፡፡

ለበለጠ መረጃ የዩኒቨርቲያችንን ድረ-ገጽ www.ecsu.edu.et እና ማህበራዊ ሚዲያዎቻችንን እንድትከታተሉ እንሳዉቃለን፡፡

**የኢትዮጵያ ፐብሊክ ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ**

**ዋና ሬጂስትራር ጽ/ቤት**